# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ

## ረቂቅ 1.0


የካቲት 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ

ማውጫ


የቃላት ፍቺ ..... iii

አሕፅሮተ-ቃላት ..... v

መ ግ ቢ ያ ..... 1

ክፍል አንድ ..... 3

የፖሊሲና ስትራቴጂ አስፈላጊነት፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ዓላማዎች ..... 3

1.1. የፖሊሲና ስትራቴጂ አስፈላጊነት ..... 3

1.2. መሰረታዊ እሳቤዎች ..... 4

1.3. ራዕይ ..... 5

1.4. ተልዕኮ ..... 5

1.5. ዓላማዎች ..... 5

1.6. የፖሊሲው የተፈጻሚነት ወሰን ..... 6

ክፍል ሁለት ..... 7

የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች ..... 7

2.2 የህግ እና ቁጥጥር ማዕቀፍ፤ ..... 8

2.2.1. የፖሊሲ መግለጫ ..... 8

2.2.2. ግቦች ..... 8

2.2.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ..... 9

2.3. የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ..... 10

2.3.1. የፖሊሲ መግለጫ ..... 10

2.3.2. ግቦች ..... 11

2.3.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ..... 11

2.4. የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ ..... 13

2.4.1. የፖሊሲ መግለጫ ..... 13

2.4.2. ግቦች ..... 13

2.4.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ..... 13

2.5. የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት ..... 15

2.5.1. የፖሊሲ መግለጫ ..... 15

2.5.2. ግቦች ..... 15

2.5.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ..... 16
2.6. ዲጂታል ማንነት እና ግላዊ መረጃ ጥበቃ ..... 18
2.6.1. የፖሊሲ መግለጫ ..... 18
2.6.2. ግቦች ..... 18
2.6.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ..... 19
2.7. ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶች ጥበቃ ..... 21
2.7.1. የፖሊሲ መግለጫ ..... 21
2.7.2. ግቦች ..... 21
2.7.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ..... 22
2.8. ሃገራዊ እና ዓለም አቀፍ ትብብር ..... 24
2.8.1. ሃገራዊ ቅንጅት እና አጋርነት ..... 24
2.8.1.1. የፖሊሲ መግለጫ ..... 24
2.8.1.2. ግቦች ..... 24
2.8.1.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ..... 25
2.8.2. ዓለም አቀፍ ትብብር ..... 26
2.8.2.1. የፖሊሲ መግለጫ ..... 26
2.8.2.2. ግቦች ..... 27
2.8.2.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች ..... 27
ክፍል ሦስት ..... 29
የፖሊሲና ስትራቴጂ የአፈፃፀም ማዕቀፍ ..... 29
3.1. አጠቃላይ ምልከታ ..... 29
3.2. ተቋማዊ መዋቅር ..... 29
3.3. የባለድርሻ አካላት ኃላፊነትና ሚና ..... 30
3.4. የፖሊሲና ስትራቴጂ ክትትል እና ግምገማ ..... 30
3.5. የፖሊሲና ስትራቴጂው ህጋዊ ጉዳዮች ..... 31
3.6. የፖሊሲና ስትራቴጂው የፋይናንስ ጉዳዮች ..... 31
3.7. የፖሊሲና ስትራቴጂ ስኬት አመላካቾች ..... 31
3.8. የፖሊሲና ስትራቴጂ ክለሳ ..... 32

# የቃላት ፍቺ

በዚህ ፖሊሲና ስትራቴጂ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር፤

1. **ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶች** ማለት በሃገሪቱ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጥቅሞች ዙሪያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ቁልፍ የሆኑ አካላዊ ወይም ቨርቹዋል ሀብቶችና ስርዓቶች ሲሆኑ፤ ጥቃት ከደረሰባቸው በህዝብ ደህንነትና ብሔራዊ ጥቅሞች ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ መሰረተ ልማቶች ናቸው፡፡
2. **የሳይበር ምህዳር** ማለት እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ መረጃዎች፣ የመረጃ መሰረተ-ልማቶች፣ መረጃ ስርዓቶች፣ መረጃን ወደ እውቀት የሚቀይርና የሚጠቀም የሰው ሃይል፤ እንዲሁም ተቋማዊና ማህበረሰባዊ ባህል ያካተተ ምህዳር ነው፡፡
3. **ዲጂታል ማንነት ጥበቃ** ማለት የሳይበር ምህዳር ተጠቃሚ ግለሰቦች፣ ዜጎች ወይም ተቋማት የመረጃ ሚስጥራዊነትና ታዓማኒነት መጠበቅ እና ያለፈቃድ አሰሳ (ብርበራ) መከላከል፤ እንዲሁም የጋራ ማንነት ጥበቃ ያካተተ ነው፡፡
4. **የሳይበር ትንኮሳ** ማለት በይነመረብን በመጠቀም የሚፈጸሙ የትኛውም አይነት ማስፈራሪያ እና ማሸማቀቂያ ድርጊቶችን ያካትታል።
5. **የሳይበር ወንጀል** ማለት የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችንና ስርዓቶችን በተለይም በይነመረብ በመጠቀም የሚፈጸም ወንጀል ነው።
6. **የሳይበር ጥቃት** ማለት በሳይበር ምህዳር የሚፈጸም ያለፈቃድ ብርበራ፣ የመረጃ ስርቆት፣ ቫይረሶችን ማሰራጨት፣ ስነ ልቦናዊ ጦርነት እና ሌሎችም የሳይበር ጥቃቶች ያካትታል።
7. **የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ** ማለት የሳይበር ደህንነትን ለማስተዳደርና ለመምራት የሚያስችል አቅጣጫ ነው።
8. **ስትራቴጂ** ማለት የፖሊሲው ተልዕኮ፣ ዓላማዎችና ግቦች እንዴት መሳካት እንዳለባቸው የሚያሳይ፤ የተፈለገውን ውጤት ለማስገኘት በስሌት የተዘጋጀ እቅድ፣ ዘዴ እና ተግባር ነው፡፡

9. **ስልት** ማለት የተነደፈው ስትራቴጂ ግቡን እንዲመታ የሚያስችል ግብዓት ሲሆን፣ ስትራቴጂው ተግባራዊ እንዲሆን የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትንም ያካትታል።

# አሕፅሮተ-ቃላት

| | |
|---|---|
| **ኢኮቴ** | ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ |
| **ኢመደኤ** | ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ |
| **ኢትዮ ሰርት** | የኢትዮጵያ የሳይበር ደህንነት ክስተት ምላሽ ሰጪ ቡድን |
| **ኢፌዲሪ** | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ |

# መ ግ ቢ ያ

በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዓለማችን በከፍተኛ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራዎች አማካኝነት እጅግ ፈጣንና ውስብስብ ለውጦችን እያስተናገደች ትገኛለች፡፡ በተለይም የሳይበር ምህዳር መፈጠር አለማችንን ወደ ትንሽ መንደር በመቀየር ሉላዊነትን አስከትሏል፡፡ ሳይበር በዋናነት በኢንተርኔት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ዓለምን በማስተሳሰር ማንኛውም ኢንፎርሜሽን ከየትኛውም የዓለም ጫፍ ተነስቶ በሰከንዶች ውስጥ በመላ ዓለም ላይ እንዲዳረስ አስችሏል፤ የሰዎችን ትስስርና ግንኙነት በቦታና በጊዜ እንዳይገደብ አድርጓል፤ ፈጣን የሆነ የመረጃ ልውውጥን ፈጥሯል፤ እንዲሁም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን በመቀየር አጠቃላይ የሰው ልጆችን የኑሮ ዘይቤ ከመሰረቱ ቀይሯል፤ አዲስ የህይወት ምዕራፍን ፈጥሯል፡፡ ምህዳሩ የሰው ልጅን እስከ አሁን ከኖረበት በጊዜና በቦታ የተገደበ አካላዊ ከሆነ ግንኙነትና የኑሮ ዘይቤ አስወጥቶ ወደ አዲስና ምናባዊ ዓለም አሸጋግሮታል፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ከሳይበር ምህዳር ውጪ መሆን የማይቻልበት፤ ያለሳይበር አቅም እንደ ሃገርና ማህበረሰብ ተወዳዳሪ ሆኖ መዝለቅ ይቅርና ህልውናን ማስጠበቅ የማይቻልበት ደረጃ ተደርሷል፡፡ ከሁሉም በላይ ሳይበር የሃገራት የህልውና ጉዳይ ሆኗል፡፡ በሳይበር ምህዳሩ ተወዳዳሪ ያልሆነ ሃገርና ማህበረሰብ ደህንነቱን በፍፁም ማስጠበቅ አይችልም፡፡ በልላ በኩል የሳይበር ምህዳር ከፍተኛ የደህንነት ስጋት እና አደጋ ያለበት ክልል ነው፡፡ በተለይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሉአላዊነትን ከማስከበር፣ የሰዎች የግል ነጻነትን (ፕራይቬሲን) ከመጠበቅ፤ እንዲሁም ከኢኮቴ ፈጣን እድገት ጋር የተያያዙ አስቸጋሪ ተቃርኖዎች ያሉበት ምህዳር ስለሆነ ደህንነቱን ማስጠበቅ የሁሉም አገራት ፈተና ሆኗል፡፡ በመሆኑም ሃገራት የምህዳሩን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፀጋዎችና መልካም አጋጣሚዎችን አሟጦ ለመጠቀም የሳይበር ደህንነት ጉዳይ ከኢኮቴ ፈጣን እድገት ትይዩ ለማስኬድ ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ እጅግ ከበለፀጉ እስከ ገና በማደግ ላይ ያሉ የዓለም ሃገራት ዘንድም የሳይበር ደህንነት ጊዜ የማይሰጠው ቀዳሚና አንገብጋቢ ጉዳይ ሆኖ ተከስቷል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የሳይበር ምህዳር በባህሪው ውስብስብ፣ የማይገመት፣ ድንበር የለሽ፣ ከፍተኛ እውቀት የሚጠይቅና ለመቆጣጠር የሚያስቸግር አውድ በመሆኑ፤ ሃገራት የሳይበር ደህንነትን በአስተማማኝ ሁኔታ ማስጠበቅ ከባድ የቤት ሥራ ሆኖባቸዋል፡፡ ሆኖም ግን የሳይበር ደህንነትን ማስጠበቅ የህልውና እንጂ የምርጫ ጉዳይ ስላልሆነ አለም አቀፍ ተቋማትና ሃገራት ደህንነቱ የተጠበቀ የሳይበር ምህዳር ለመፍጠር ሌት ተቀን እየታተሩ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ምክንያትም ብዙ ሃገራት የሳይበር ምህዳሩን ለማስተዳደርና ለመምራት ያስችላቸው ዘንድ ፖሊሲና ስትራቴጂ ያወጣሉ፡፡

ሃገራችን ኢትዮጵያ ልክ እንደ ሌሎች ሃገራት ከኢንፎርሜሽንና ኮምኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶች መስፋፋት ትይዩ የሚከሰቱ እድሎችና የደህንነት ፈተናዎችን እያስተናገደች ትገኛለች፡፡ በተለይም ከላይ የተጠቀሱት ያደጉ አገራትም ጭምር ከሚፈታተኑ ተቃርኖዎች በተጨማሪ ኢትዮጵያ ሌሎች ተጨማሪ የሳይበር ደህንነት ተቃርኖዎች አሉባት፡፡ ይህ ማለት አገሪቱ ካላት ውስን ሀብት፣ ከቴክኖሎጂ ጥገኝነትና ከፍተኛ ተጋላጭነት፣ ዝቅተኛ ከሆነው የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና፣ ካለው ከፍተኛ የሙያተኛ እጥረት እና ያልዳበረ የምርምር ሥራ አንፃር ከፍተኛ የሳይበር ደህንነት ስጋት እንዲኖራት አድርጓታል፡፡

በመሆኑም እነዚህን ተቃርኖዎች ግንዛቤ ውስጥ ያስገባና ዘመኑን የዋጀ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ በ2004 ዓ.ም የወጣውን የኢንፎርሜሽን ደህንነት ፖሊሲ በማሻሻል ይህ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ሊዘጋጅ ችሏል፡፡

# ክፍል አንድ

# የፖሊሲና ስትራቴጂ አስፈላጊነት፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ዓላማዎች

## 1.1. የፖሊሲና ስትራቴጂ አስፈላጊነት

ፖሊሲና ስትራቴጂው ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሊዘጋጅ ችሏል፡-

1. ብሄራዊ የሳይበር ደህንነት ሁኔታ ከኢኮቴ መስፋፋት ጋር ተያይዞ አጠቃላይ መልኩና ባህሪው ከመቀየሩ የተነሳ የአንድን አገር ሉአላዊነትና ደህንነት በአግባቡ ማስጠበቅ የማይቻልበት ጊዜ ደርሰናል፤ ኢትዮጵያም እጅግ ውስብስብ፣ ተለዋዋጭና ኢ-ተገማች የሆነውን እና በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚታገዘውን የሳይበር ደህንነት ለማስጠበቅ በርካታ መልካም አጋጣሚዎች ለመጠቀም፣ እንዲሁም ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችል ዘመኑንና ምህዳሩን የሚመጥን ፖሊሲና ስትራቴጂ የሚያስፈልጋት በመሆኑ፤
2. ከመቼውም ጊዜ በላይ የሳይበር ምህዳር በኢትዮጵያ የማህበረ-ባህላዊ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የደህንነት ጉዳዮች ላይ ጉልህ ድርሻ እየያዘና ተጨባጭ ተፅዕኖ እየፈጠረ የሚገኝ በመሆኑ፤ ይህንን ታሳቢ ያደረገ የሳይበር ደህንነት የፖሊሲ ግቦችንና አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤
3. የሀገሪቱን ውድ ኢንፎርሜሽን እና ኢንፎርሜሽን የሚከማችበት፣ የሚተነተንበትና የሚሰራጭበት ቁልፍ መሰረተ-ልማቶች መስፋፋትና እድገት ጋር ተያይዞ የሚመጡ የደህንነት ስጋቶችና ተጋላጭነቶች በመጨመራቸው፤
4. የሳይበር ደህንነት በባህሪው የመንግስት ሀላፊነትና ድርሻ ብቻ ተደርጎ የሚወሰድ ባለመሆኑ የተቀናጀ የመንግስት፣ የግል፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሚኖራቸው ተሳትፎና አስተዋፆ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የግል ዘርፉ ሊኖረው ከሚችል እምቅ አቅም ጋር ተያይዞ በሌላው ዓለም ካለው ተጨባጭ እውነታና በአገራችንም የግሉ ዘርፍ እድገት ተከትሎ የመንግስት ቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማት በዘርፉ እየተያዙ በመሆናቸው የመንግስትንና የግሉ ዘርፍ በሳይበር ደህንነት ላይ የሚኖራቸውን

ተመጣጣኝና ተመጋጋቢ ሚና ከግምት ውስጥ ያስገባ አስተሳሰብና አሰራር ለማስተዳደርና ለመምራት፤

5. የሀገራችን የሳይበር ምህዳር ባህሪይና የደህንነት ስጋትና ተጋላጭነት አንጻር ዓለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ ለማወቅና ለመጠቀም፤ በሃገሪቱ ተቀባይነት ያገኙ የህግ ማዕቀፎችና የቁጥጥር ስታንዳርዶችንና መለኪያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ፤ ከስነ-ምህዳሩ ጋር አብሮ መራመድ የሚያስችል የጥናትና ምርምር አቅም ለመገንባት፤ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ለማሳደግ፤ እንዲሁም ከምህዳሩ ጋር የሚጣጣሙ የፖሊሲ አቅጣጫዎች፣ ስትራቴጂዎችና ስልቶች መንደፍ እና የፖሊሲው አፈፃፀም የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ለመዘርጋትና ተጠያቅነት እንዲኖር ለማስቻል፤

## 1.2. መሰረታዊ እሳቤዎች

1. **የመንግስት ቁርጠኛ አመራር**

   የተቀናጀ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ሀብቶች እና አቅሞች ስምሪት እንዲረጋገጥ ለፖሊሲው አፈጻጸም መንግስት ስትራቴጂክ አመራር ይሰጣል፤

2. **የጋራ ኃላፊነት**

   የሳይበር ደህንነት የሁሉም አካላት የጋራ ኃላፊነት ስለሆነ ዜጎች፣ መንግስት እና የግል ዘርፉ በከፍተኛ የባለቤትነት ስሜት ተግባራዊ እንዲሆን በትብብር እና በጋራ በኃላፊነት የሚፈፅሙት ይሆናል፤

3. **የህግ የበላይነት**

   እምነት የሚጣልበት የሳይበር ምህዳር ለመፍጠር፣ የዜጎች ህገ መንግስታዊ መብት፣ ነፃነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በገሃዱ ዓለም ተግባራዊ እንደሚሆነው ሁሉ በከፍተኛ ትስስር ውስጥ ባለው የሳይበር ማህበረሰብ የህግ የበላይነት የማረጋገጥ ስራ ቁልፍ ተግባር እንደሆነ ተወስዶ ይተገበራል።

4. **ዓለም አቀፋዊ ትብብርና አጋርነት**

የሳይበር ስጋትና ጥቃት ድንበር ተሻጋሪ ባህሪ ያለው በመሆኑ ጠንካራ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ትብብር እና አጋርነት አቅም በአገር ደረጃ ይገነባል፤

5. **የኢትዮጵያ እሴቶች**

የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ እሴቶችን በጠበቀ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል፤

### 1.3. ራዕይ

ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የሀገሪቱን ዜጎች፣ የመንግስት እና የግል ተቋማትን ደህንነት ማስጠበቅ የሚያስችልና የማይበገር የሳይበር ደህንነት አቅም ተገንብቶ ማየት፡፡

### 1.4. ተልዕኮ

የሃገሪቱን ኢንፎርሜሽን እና ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶችን ከሳይበር ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል በራስ አቅም ላይ የተመሰረተ የሳይበር ደህንነት አቅም በመገንባት ብሄራዊ ጥቅሞችን ማስጠበቅ፤

### 1.5. ዓላማዎች

1. የሳይበር ደህንነት ስጋት እና ተጋላጭነት የመከታተል፣ ቀድሞ የመለየት፣ የማስጠንቀቅ፣ የመከላከል እና ፈጣን ምላሽ የመስጠት፤ ጥቃት ሲደርስ በፍጥነት መልሶ መቋቋም የሚያስችል የማይበገር የሳይበር ደህንነት አቅም መገንባት፤
2. የሳይበር ደህንነት በሂደቱና በውጤቱ ለዜጎች የግል ነፃነትና ሰብአዊ መብት መከበር፤ ለዲሞክራሲ መብቶች፤ እንዲሁም ለዘላቂ ሰላምና ልማት መረጋገጥ ሚና እንዲኖረው ማስቻል፤
3. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ጠንካራ ሃገራዊ፣ ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ አጋርነቶች እና ትብብሮችን መፍጠር፤
4. ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የምርምርና ልማት ተግባራት በማከናወን፤ የቁልፍ መሰረተ-ልማቶች እና የኢንፎርሜሽን ሀብቶች ደህንነት በዘላቂነት

የሚያስጠብቁ ሃገር በቀል የቴክኖሎጂ አቅሞች እና የአሰራር ስርዓቶች መገንባትና መዘርጋት፤

5. ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ባህልን በመገንባት የሳይበር ምህዳርን በእውቀት የሚጠቀም፣ ምክንያታዊና የነቃ ማህበረሰብ መፍጠር፤

## 1.6. የፖሊሲው የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በሃገሪቱ በሚገኙ በሁሉም የመንግስት እና የግል ተቋማት የሚተገበር ሲሆን በየተቋማቱ የሚገኝ ኢንፎርሜሽን፣ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችን እና ስርዓቶችን የሳይበር ደህንነት ስጋትና ተጋላጭነትን መቀነስ፣ እንዲሁም የሳይበር ጥቃትን መከላከል ላይ ያተኩራል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች

## 2.1 የፖሊሲ ጉዳዮች

በሳይበር ዓለም የሃገራትን ሉዓላዊነት ማስጠበቅ ፈታኝ ጉዳይ ሆኗል፡፡ በተለይም ዓለም ዓቀፋዊ ባህሪ ባለው የሳይበር ዓለም ውስጥ ተወዳዳሪ አቅም ያልገነባ ሃገር የሳይበር ሉዓላዊነቱ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ጥያቄ ውስጥ ይገባል፡፡ ይህም የሚሆነው በሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ቀዳሚ የሆኑ ሃገራት ቴክኖሎጂውን በቀላሉ አሳልፎ የማይሰጡ ከመሆኑም ባሻገር የቴክኖሎጂው ባህሪ በተፅዕኖ ሥር ለማዋል አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ ነው፤ በዚህም ወደ ኋላ ቀሪ ሃገራት በእጅጉ ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ በሌላ በኩል የሳይበርን ዓለም አለመቀላቀል አማራጭ ባለመሆኑ ሃገራት ቢዘጋጁም ባይዘጋጁም የሳይበርን ዓለም መቀላቀላቸው የግድ በመሆኑ የዚሁ የግሎባላይዜሽን አካል ሆነዋል፡፡ በመሆኑም ሃገራት የዘርፉን ቴክኖሎጂ አቅም ከማጎልበት ጎን ለጎን የቁጥጥር ሥርዓቶችን በማበጀት የሳይበር ደህንነት ክፍተቶችን ለመቆጣጥር ይጥራሉ፡፡

ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ካሉት ሃገራት ተርታ የምትመደብ ቢሆንም ከሳይበርና ከቴክኖሎጂው ጋር አብሮ ከሚመጣው የደህንነት ተጋላጭነት ማምለጥ አትችልም፡፡ ይህም በመሆኑ የደህንነት ቴክኖሎጂውን በምርምርም ሆነ በግዥም ከመታጠቅ ባሻገር የቁጥጥር ሥርዓት በማበጀት የሳይበርን ጥቃት የመከላከል አቅሟን ማሳደግ ይገባታል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ በሳይበር ዓለም ያሉ ተቃርኖዎችን በመገንዘብ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት መገንባት ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ፖሊሲው ሰባት አንኳር የትኩረት አቅጣጫዎችን አካቷል፡፡ እነዚህም ህግና ቁጥጥር፣ ንቃት ህሊና፣ የአቅም ግንባታ፣ ምርምርና ኢኖቬሽን፣ ኦንላይን የግላዊ መብት እና የሰብዓዊ መብት ጥበቃ፣ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ጥበቃ እና ዓለም ዓቀፍና ሃገራዊ ትብብር ናቸው፡፡

## 2.2 የህግ እና ቁጥጥር ማዕቀፍ፤

### 2.2.1. የፖሊሲ መግለጫ

በአሁኑ ወቅት እየተስፋፋ የሚገኘውን የሳይበር ተጋላጭነትና ስጋት ለመቀነስ፣ ጥቃት ለመከላከል፤ እንዲሁም አጥፊዎችን ተጠያቂ ለማድረግ ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም እና ወቅታዊ የሆነ የህግ እና ቁጥጥር ማእቀፍ ማዘጋጀትና መተግበር ተገቢ ነው፡፡ የኢትዮጵያን የሳይበር ደህንነት ለመጠበቅ፤ ድንበር የለሽ የሳይበር ወንጀሎች፣ ሽብርተኝነት፣ የሳይበር ስለላ፣ ከሌሎች ሀገራት የሚሰነዘሩ የሳይበር ጥቃቶች እና የመሳሰሉትን ለመከላከል የሚያስችሉ የሳይበር ደህንነት ህጎች፣ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስታንዳርዶች እና የቁጥጥር ማዕቀፎች ማልማትና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም የሃገራችንን የሳይበር ደህንነት የሚያስጠብቁ ሕግጋት እና የቁጥጥር ማዕቀፎች ማልማቱ፣ ማጽደቁ እና ተፈጻሚ ማድረጉ የሳይበር ተጋላጭነትና ስጋት ከመቀነስ ባሻገር የሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነቶቻቸውንና ግዴታዎቻቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም የሃገሪቱን ብሄራዊ የሳይበር-ምህዳር እና ቁልፍ መሰረተ-ልማቶችን ደህንነት ለማስጠበቅ፣ ከጥቃት ለመከላከል፣ ጥቃት ሲፈጸም ምላሽ ለመስጠት፣ ለሕግ ለማቅረብ እና የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ በማህበረሰቡ ዘንድ እንዲሰርጽ ለማድረግ፤ የሚከተሉት የህግና ቁጥጥር ግቦች፣ ስትራቴጂዎችና ስልቶች ይነደፋሉ፤ ይተገበራሉ፡፡

### 2.2.2. ግቦች

የህግ እና ቁጥጥር ማዕቀፍ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

1. የሳይበር ደህንነት ስጋቶችንና ተጋላጭነቶችን መቀነስ፤ ጥቃቶችን ለመከላከል እና ለመቋቋም የሚያግዙ፤ እንዲሁም ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸው ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ህጎች እና ስታንዳርዶች ጋር ተጣጣሚነት ያላቸው የሳይበር ደህንነት ሕግጋት እና ቁጥጥር ማዕቀፎችን ማውጣት፤ በቀጣይነትም ማሻሻል፤

2. የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ የሳይበር ስለላ እና መሰል ጥቃቶች ለመከላከል የሚያስችል የህግ አካላትን አቅም መገንባት፤

3. በሀገር ውስጥ የሚመረቱና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የሳይበር ደህንነት ምርቶችና አገልግሎቶች፤ እንዲሁም ቁልፍ የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎች ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ፍላጎትን ያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፤

4. ማህበረሰቡ በሀገሪቱ የሳይበር ደህንነት አቅሞች ዙሪያ ያለውን ዓመኔታ ለማሳደግ በኢንፎርሜሽን አሰባሰብ፣ ትንተና፣ ስርጭት፣ አጠቃቀም፣ ክምችት እና አወጋገድ ዙሪያ ደረጃቸውን የጠበቁ የህግና ቁጥጥር ማዕቀፎችን መዘርጋት፤

### 2.2.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. ከሃገራዊ ተጨባጭ የሳይበር ደህንነት ሁኔታዎች ጋር የተጣጣሙና ወቅታዊነታቸውን የጠበቁ መሰረታዊና የሥነ-ስርዓት ሕጎች እና የቁጥጥር ስርዓቶች ማዘጋጀት እና ማሻሻል፤

    **ስልት አንድ፡** በመንግስት እና በቁልፍ የግል ተቋማት ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ስታንደርዶች እና የአሰራር ስርዓቶች መቅረጽ፣ መተግበር፤

    **ስልት ሁለት፡** የሳይበር ደህንነት ሕግጋትና የቁጥጥር ማዕቀፎች ተቀባይነት እና ተፈፃሚነት ለማሳዳግ በሂደቱ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ እንዲሰራ ይደረጋል፤

2. በሳይበር ደህንነት ህግጋትና ቁጥጥር ማዕቀፎች ዙሪያ ብቁ የህግ አውጪዎችን፣ የህግ አስፈፃሚዎችንና ተርጓሚዎችን በመፍጠር፤ በቀጣይነት አቅም መገንባት፤

**ስልት፡** የሳይበር ደህንነት ህጎችን ለማስፈጸም የመርማሪዎች፣ አቃቤ ህጎች፣ ዳኞች እና ሌሎች የፍትህ አካላት በትምህርት፣ በስልጠና፣ በምክክር መድረኮች፣ በኮንፈረንሶችና በመሳሰሉት ዘዴዎች አቅማቸው በቀጣይነት ይገነባል፤

3. ከሳይበር ደህንነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ከማቅረብና ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ምርቶችን ከማስወገድ ጋር የተያያዙ የጥራትና ቁጥጥር ስታንዳርዶች እና መለኪያዎች መቅረጽ፤

**ስልት፡-** በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ የሚገቡ የሳይበር ደህንነት ምርቶች ጥራትና ብቃታቸው ይፈተሻል፤ የፈጻሚ አካሉን በቀጣይነት የማብቃት ስራዎች ይሰራሉ፤

4. የኢንፎርሜሽን ሚስጢራዊነት፣ ተደራሽነትና ተዓማኒነት ለማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ ህገ ወጥ የሳይበር ድርጊቶችን ተከታትሎ ለሕግ በማቅረብ የማህበረሰቡን ንቃተ-ህሊና ማሳደግ፤

**ስልት፡-** ከሳይበር ደህንነት ህግጋትና ቁጥጥሮች ዙሪያ ማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረው የንቃተ-ህሊና ስራዎች ይሰራሉ፤

## 2.3. የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና

### 2.3.1. የፖሊሲ መግለጫ

የሳይበር ደህንነት የቴክኖሎጂ፣ የስራ ሂደትና የሰው ልጅ መስተጋብር ውጤት ሲሆን በተለይም የመንግስትና የግል ተቋማት እና ዜጎች በእውቀትና በአመለካከት ማነስ፤ እና በተግባር ክፍተት ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን የሳይበር ደህንነት ስጋት፣ ተጋላጭነትና ጥቃት ለመከላከል የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ማጎልበት ተገቢ ነው። በሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከቁልፍ መሰረተ-ልማት እድገትና ከኢንፎርሜሽን ተጠቃሚነት አንጻር ሲታይ የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ጉዳይ በቂ ትኩረት ያልተሰጠውና በዘርፉ ያለው የግንዛቤ ደረጃም እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡

ስለሆነም በሀገሪቱ በሳይበር ደህንነት አካላት ዘንድ የሳይበር ስጋቶችንና ተጋላጭነቶችን ለመቀነስ የህብረተሰቡ ንቃተ-ህሊና ከፍ በማድረግ፣ የመረጃ ዋጋና የሳይበር ደህንነት ጥቃት አስመልክቶ በእውቀት ላይ የተመሰረተ የመረጃ ልውውጥ ባህል እንዲጎለብት፣ እንዲሁም የአመለካከትና የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ መንግስት የሚከተሉትን ግቦች፣ ስትራቴጂዎችና ስልቶችን መነሻ በማድረግ የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና እንዲዳብር ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፡፡

### 2.3.2. ግቦች

የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

1. የመንግስት ተቋማት፣ የግል ተቋማትና ዜጎች በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ያላቸውን እውቀትና አመለካከት ማዳበር፤
2. ከጥንቃቄ ጉድለትና ካለማወቅ የሚደርሱ የሳይበር ጥቃቶች፣ ስጋቶች እና ተጋላጭነቶችን መቀነስ፣
3. የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶችና ስጋቶች ለመቀነስ፤ እንዲሁም ጥቃቶች ለመከላከል የሚያስችል የዜጎች ንቃተ-ህሊና ማሳደግ እና ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ባህል መፍጠር፤

### 2.3.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ማሳደግ የሚያስችሉ ተቋማዊ መዋቅሮችና የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት፤

**ስልት አንድ፡** በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የተሰማሩ ተቋማት ተደራሽነታቸውን በማስፋትና በማጠናከር ለህብረተሰቡ የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ መስጠት፤

**ስልት ሁለት፡** በሳይበር ደህንነት ክስተቶች ዙሪያ ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚያስችሉ የጥሪ ማዕከልና ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራዎች ይሰራሉ፤

**ስልት ሶስት፡** በትምህርት ተቋማት የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ክበቦች ይቋቋማሉ፤

2. በመንግስት እና በግል ተቋማት ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ደረጃቸውን የጠበቁ ብሄራዊ የሳይበር ደህንነት የንቃተ ህሊና ማዕቀፎችና ፕሮግራሞች መቅረጽና ማበልጸግ፤

    **ስልት አንድ፡** በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የተሰማሩ ተቋማትን በማስፋትና በማጠናከር ለህብረተሰቡ ወቅታዊ የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ እንዲሰጡ ይደረጋል፤

    **ስልት ሁለት፡** በሀገሪቱ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ተቋማት በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ወቅታዊና ቀጣይነት ያለው የምክክር መድረኮች፣ ፓነሎች፣ ውይይቶች እና የመሳሰሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ይዘጋጃሉ፤

    **ስልት ሶስት፡** ብሄራዊ የሳይበር ደህንነት ሳምንት በማክበር ሃገር አቀፍ የንቃተ-ህሊና ማጎልበቻ ዘመቻዎች ይከናወናሉ፤

3. የመገናኛ ብዙሃን የመረጃ ዋጋና መሰረታዊ የሆኑ የሳይበር ደህንነት ባህሪያትና የማስጠበቂያ እና የማስገንዘቢያ ስርዓቶች እንዲኖራቸው ማድረግ፤

    **ስልት አንድ፡** የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የህብረተሰቡ ንቃተ-ህሊና እና ግንዛቤ ለማሳደግ የተለያዩ ወቅታዊነታቸውን የጠበቁ የሳይበር ደህንነት ፕሮግራሞች ይዘጋጃሉ፤ ይቀርባሉ፤

    **ስልት ሁለት፡** በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ለሚሰሩ ለመገናኛ ብዙሃን፣ ለግል ተቋማት፣ ለሲቪክ ማሕበራት እና ሌሎች አካላት እውቅና እና ማበረታቻ ይሰጣል፤

## 2.4. የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ

### 2.4.1. የፖሊሲ መግለጫ

በሀገራችን ከሳይበር ደህንነት ጋር በተያያዘ በቂ የሆነ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና ጠንካራ የሳይበር ደህንነት የአሰራር ስርዓቶችና ተቋማዊ መዋቅሮች ባለመኖራቸው ምክንያት የሳይበር ደህንነት አቅም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲሆን አስተዋጽኦ አድርጓል። ከዚህ የተነሳ የሀገሪቱ ዜጎች፣ የመንግስትና የግል ተቋማት ለተለያዩ ጥቃቶች ተጋላጭ እንዲሆኑ፤ እንዲሁም ከሳይበር ምህዳር ማግኘት የሚገባቸው ጥቅም ሊያገኙ አልቻሉም። በመሆኑም ጠንካራ የሆነ የሳይበር ደህንነት አቅም መገንባት መቻል ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ዕድገት እና ለውጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ስለሆነ መንግስት በህብረተሰቡ ዘንድ ጠንካራ የሳይበር ደህንነት ባህል ለመገንባት፤ የትምህርት እና ስልጠና ፕሮግራሞች ለማስፋፋት፤ ተቋማዊ/ መዋቅራዊ አቅሞች እና የአሰራር ስርዓቶች ለመገንባት በሃገር ደረጃ የማይበገር እና ተጣጣፊ የሆነ የሳይበር ደህንነት አቅም ለመገንባት የሚከተሉትን ግቦች፣ ስትራቴጂዎች እና ስልቶች በማስቀመጥ ይሰራል።

### 2.4.2. ግቦች

የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

1. የሳይበር ደህንነት ስጋት፣ ተጋላጭነት እና ጥቃት ለመለየት፣ ለመዳሰስ እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ተቋማዊ መዋቅሮችንና አቅሞችን መገንባት፤
2. የመንግስት፣ የግል እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሳይበር ደህንነት አቅማቸውን ማጠናከር፤
3. በሀገር ደረጃ ብቃት ያላቸው የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችን መፍጠር፤

### 2.4.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. በሀገሪቱ ደረጃቸውን የጠበቁ የሳይበር ደህንነት ትምህርት እና ስልጠና ፕሮግራም እንዲኖር በማድረግ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ፤ እንዲሁም

በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በዘርፉ የትምህርትና ስልጠና ስርዓተ-ትምህርት መቅረፅ፤

**ስልት አንድ፡** የሳይበር ደህንነት ትምህርት በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ውስጥ ይከተታል፣

**ስልት ሁለት፡** የሳይበር ደህንነት አቅም ለማሳደግ የሚረዱ ወቅታዊ የሆኑ የትምህርትና ስልጠና ሰርትፊኬሽኖች ለባለሙያዎች ይሰጣል፤

**ስልት ሶስት፡** የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችን ሊያሰራ የሚችል የብቃት መመዘኛ ስታንዳርድ ማስቀመጥ፤

2. ውጤታማ የሆነ የሳይበር ደህንነት የእውቀት አስተዳደር እና ስርጭት ስርዓት በሃገር ደረጃ መዘርጋት፤

   **ስልት፦** የመንግስትና የግል ተቋማት እንዳስፈላጊነቱ የሳይበር ደህንነት የአሰራር ስርዓቶች ይተገብራሉ፤

3. የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ ለማረጋገጥ የሚያስችል እውቀት እና ክህሎት የተላበሰ ተቋማዊ መዋቅሮች እና አሰራር ስርዓቶች መዘርጋት፤

   **ስልት፡** በመንግስት፣ በግልና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የምርጥ ተሞክሮ፣ የልምድ ልውውጥና፣ የእውቀት ሽግግር ለማድረግ የሚያስችሉ መድረኮች ይዘጋጃሉ፤

4. ብሄራዊ ጥቅሞችን የሚያስጠብቁ የፈጠራ ችሎታ እና ተሰጥኦ መሰረት ያደረጉ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ ጠንካራ እና ቀጣይነት ያለው ብቁ የሆነ የሰው ኃይል መፍጠር፤

   **ስልት አንድ፡** በቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ተቋማት ውስጥ በሚሰሩ ባለሙያዎች ስብዕና ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት የምልመላ እና የማብቃት ስራ ይሰራል፤

ስልት ሁለት፡ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በዘርፉ ከተሰማሩ ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር የልምድ ልውውጥ እና የእውቀት ሽግግር ይደረጋል፤

## 2.5. የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት

### 2.5.1. የፖሊሲ መግለጫ

የሳይበር ምህዳር ባህሪው እጅግ ውስብስብ፣ ተለዋዋጭ እና ኢ-ተገማች በመሆኑ በመስኩ ዕውቀት፣ ክህሎት እና ግኝቶችን ለማዳበር፤ የሳይበር ደህንነት አቅም በመገንባት ረገድ ነባሩን በማሻሻል እና አዳዲስ መፍትሄዎችን በማበልጸግ ተከታታይ የምርምር እና የልማት አቅሞችን ማዳበር የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ ጠቃሚ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የሳይበር መሰረተ ልማቶችንና ቴክኖሎጂዎች በማበልጸግ፣ የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ ሽግግሮች እና አዳዲስ ፈጠራዎች በማስፋፋት፤ እንዲሁም በተለያዩ ደረጃዎች ሃገር በቀል እና አለም አቀፍ ምርምር እና ልማት ተግባራት ሊከናወኑ ይገባል፡፡ በመሆኑም መንግስት በዘርፉ የራስ አቅም እንዲኖር፣ የሳይበር ቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ስራዎች በተደራጀ ጥናት እና ምርምር በመደገፍ የሳይበር ደህንነት ኢንዱስትሪ ለመገንባት ይሰራል፡፡ ይህንን ለማሳካት የሚከተሉት ግቦች እና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችን በመለየት በልዩ ትኩረት መንግስት ይንቀሳቀሳል።

### 2.5.2. ግቦች

የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፦

1. ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ምርቶችና አገልግሎቶች በምርምርና ልማት ላይ የተመሰረቱ ማድረግ፤
2. የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶች፣ ስጋቶች እና ጥቃቶች መንስዔዎቻቸውን በጥናትና ምርምር መለየት፤ መፍትሄዎች ማቅረብ፤
3. የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ ሃገር በቀል ዕውቀት እና ፈጠራዎችን መሰረት ያደረገ የምርምር እና ልማት አቅም መገንባት፤

4. በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ እና የተቀናጀ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት ባህል መገንባት፤

### 2.5.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ሃገራዊ አሻራ ያላቸው ምርት እና አገልግሎት አቅርቦትን በጥናት እና ምርምር መደገፍ፤

   **ስልት ሶስት፦** ቁልፍ የመሰረተ ልማቶች ከጥቃት መከላከል የሚያስችሉ በጥናት እና ምርምር የተለዩ ሀገራዊ አሻራ ያላቸው አስፈላጊ ቴክኖሎጂዎች ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ይደረጋል፤

   **ስልት ሶስት፦** አዳዲስ ምርት እና አገልግሎቶች በዘርፉ እንዲበራከቱ የሳይበር ደህንነት ምርምርና ልማት ለማጠናከር የተለያዩ ማበረታቻዎች ይሰጣሉ፤

2. ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ከሳይበር ኢንዱስትሪ ጋር ትብብር እና አጋርነት በመፍጠር የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት አቅም መገንባት የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ማስፋፋት፤

   **ስልት አንድ፦** የምርምርና ልማት ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል እውቀት፣ ክህሎት፣ ልምድ እና የቴክኖሎጂ አቅም ይገነባል፤

   **ስልት ሁለት፦** በተለያዩ የምርምር ተቋማት፣ የደህንነት ተቋማት እና ዩኒቨርሲቲዎች የሳይበር ደህንነት እንዳስፈላጊነቱ የልህቀት ማዕከላት ይቋቋማል፤

   **ስልት ሶስት፦** በሳይበር ምህዳር ውስጥ ባሉ ተዋናዮች መካከል ያለው ትብብር በማጠናከር የተቀናጀ የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ወቅታዊነታቸውን የጠበቁ የእውቀትና የልምድ ልውውጥ መድረኮች፣ ኮንፈረንሶችና ፕሮግራሞች ይካሄዳሉ፤

**ስልት አራት፦** የሳይበር ደህንነት የምርምር እና ልማት ተግባራትን ከሚመለከታቸው የመንግስትና የግል ተቋማት እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ይፈጸማል፤

3. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ ተጨማሪ እሴት ያላቸው ምርቶችና አገልግሎቶች የሚሰጡ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤ የምርምርና ልማት ተቋማት መገንባት፤

    **ስልት አንድ፦** ብሄራዊ የምርምርና ልማት ፍኖተ-ካርታ ለሳይበር ደህንነት በማዘጋጀት ይሰራል፤

    **ስልት ሁለት፦** ምርምር እና ፈጠራ የሚያበረታቱ የሳይበር ደህንነት ጋር የተያያዙ ፕሮግራሞችን ይቀረፃሉ፤

4. የመንግስት፣ የዜጎች እና የግል ተቋማትን መረጃዎች ከሳይበር ተጋላጭነትና ጥቃት በመጠበቅ፣ ጥቃት ሲደርስ አጸፋዊ ምላሽ በመስጠት፣ ከጥቃት በፍጥነት እንዲያገግሙ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በምርምርና ልማት መደግፍ፤

    **ስልት አንድ፦** የግል ሴክተሩ በአገሪቱ የሳይበር ደህንነት ምርምር እና ልማት ፕሮግራሞች እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤

    **ስልት ሁለት፦** ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶችን ተጋላጭነትና ጥቃት ለመከላከል በሚያስችል ሁኔታ በቀጣይነት በምርምርና ልማት ይደገፋል፤

5. ከሳይበር ደህንነት ጋር በተያያዘ በሃገሪቱ ልዩ ትኩረት በተሰጣቸው ወቅታዊ እና ታሳቢ የሳይበር ደህንነት ስጋቶች በጥናትና ምርምር መደገፍ፤

    **ስልት አንድ፦** በብሄራዊ ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ በሳይበር ደህንነት ጉዳዮች ዙሪያ ልዩ ትኩረት በመስጠት የምርምር እና የልማት ተግባራት ይከናወናሉ፤

    **ስልት ሁለት፦** በሃገሪቱ ለስጋት ሀይሎች ጥቃት የማይበገር የሳይበር ክልል እንዲኖር ጠንካራ የሆነ የሳይበር ደህንነት እንዱስትሪ ለመገንባት በጥናትና ምርምር ይደገፋል፤

## 2.6. ዲጂታል ማንነት እና ግላዊ መረጃ ጥበቃ

### 2.6.1. የፖሊሲ መግለጫ

ዲጂታል ማንነት እና ግላዊ መረጃዎች ተገቢ የሆነ ትኩረት እና ጥበቃ ካልተደረገላቸው በዜጎች ላይ የሚደርስ የሳይበር ጥቃት እንዲስፋፋ፣ ማንነት ተኮር ጥቃቶች እንዲበራከቱ፣ እንዲሁም ከማህበረሰቡ ባህልና እሴት ያፈነገጡ ክስተቶች የዜጎች የግል ሕይወትና ሰብዓዊ መብቶች ስጋት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል። ስለሆነም መንግስት በዜጎች ላይ ያነጣጠሩ የስነ-ልቦና ጥቃቶች ለመከላከል፣ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ፣ የዲጂታል ማንነትና የግላዊ መረጃ ስጋትና ተጋላጭነት ለመቀነስ፣ እንዲሁም ዜጎች ለግል መረጃ ልውውጥ የሚጠቀሟቸውን የኢንፎርሜሽን መሰረተ- ልማቶች ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግቦች እና ስትራቴጂዎችን ነድፎ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ይሰራል።

### 2.6.2. ግቦች

የዲጂታል ማንነትና ግላዊ የመረጃ ጥበቃ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

1. በዜጎች ዘንድ ታዓማኒነት ያለው የዲጂታል አገልግሎት እና ግላዊ መረጃ ጥበቃ እንዲኖር ማድረግ፣
2. በታዳጊዎች ላይ የሚደርሱ የሳይበር ስጋቶችን፣ ተጋላጭነቶችንና ጥቃቶችን መከላከል፣ በኢትዮጵያ ማህበረሰብ እሴቶችና በመልካም ስብዕና ታንፀው እንዲያድጉ ሳይበር ሊጫወተው የሚገባ ገንቢ ሚና ማሳደግ፣
3. በሳይበር ምህዳር ላይ የሚደርስ ጾታዊ ጥቃት፣ ወሲባዊ ትንኮሳ፣ የሥነ-ልቦና ተፅዕኖ መከላከል እና መቀነስ፣
4. ማንነትን መሰረት ያደረጉ በዲጂታል የሚፈጸሙ የሃይማኖት ጽንፈኝነት፣ የብሄር ተኮር ጥቃቶችንና የመሳሰሉትን መግታትና መከላከል፣

### 2.6.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. የዲጂታል ማንነትና ግላዊ መረጃ ለመጠበቅ የሚያስችሉ አስገዳጅ ህጎች ስታንዳርዶች እና ደንቦች፤ እንዲሁም ሌሎች አጋዥ የሚባሉ የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት፤

   **ስልት አንድ፡-** የግላዊ መረጃ ደህንነት ማረጋገጥ የሚያስቸሉ አቅሞች፣ ተቋማዊ ማዕቀፎች፣ የህግ እና የቁጥጥር አሰራር ስርዓቶች በቅንጅት ተግባራዊ ይደረጋል፤

   **ስልት ሁለት፡-** አስተማማኝ የሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂ እና ገለልተኛ የዳታ ፕራይቪሲ ህግ ማስተዋወቅ፣ ህጋዊ የመረጃ አሰባሰብ አሰራር እና መቆጣጠርያ መመሪያ ይዘጋጃል፤

   **ስልት ሶስት፡-** በግላዊ መረጃ ጥበቃ እና በሳይበር ደህንነት ማረጋገጥ መከካል ያሉ ተቃርኖዎችን ለማስታረቅ የሚያስችሉ አሰራሮች ይተገበራሉ፤

2. ተቋማት የግለሰቦችን መረጃ በሚሰበስቡበት ወቅት ግላዊ መረጃ ስምምነት እና መተማመን በመፍጠር መሰብሰብ፣ ለሚከማች መረጃ ጥበቃ የማድረግ፣ ገደብ የማስቀመጥ፣ የተጠያቂነት እና የህጋዊነት ስታንዳርዶች እና የቁጥጥር ስርዓቶች ይተገበራል፤

   **ስልት አንድ፡-** የግለሰቦች መረጃ የሚሰበስቡ፣ ፕሮሰስ የሚያደርጉ እና የሚያከማቹ ተቋማት ምን ዓይነት ኢንፎርሜሽን፣ ከማን፣ እንዴት መሰብሰብ፣ ፕሮሰስ ማድረግ፣ መጠቀም፣ ማከማቸት፣ እና ማስወገድ እንዳለባቸው በየጊዜው የማንቃት ስራ ይሰራል፣

   **ስልት ሁለት፡-** መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በልዩ ሁኔታ የግለሰቦችን ግላዊነት መብት መጠበቅ የሚያስችል አሰራር በሚያወጧቸው የሳይበር ደህንነት ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ደንቦች እና ሌሎች የአሰራር ስርዓቶች እንዲካተቱ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፡

**ስልት ሶስት፡-** የሚመለከታቸው ተቋማት የዜጎችን ግላዊ መረጃ በተመለከተ በቀጣይነት ክትትል እና የትንተና ስራ ተግባራዊ ይደረጋል፤

**ስልት አራት፡-** ኤሌክትሮኒክ የመንግስት አገልግሎቶች ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ይደረጋል፤

3. ዲጂታል ማንነት እና ግላዊ መረጃ ለማስከበር ጠንካራ የሆነ የዓለም አቀፍ ትብብር እና አጋርነት መመስረት፤

   **ስልት አንድ፡** ሃገሪቱ በዲጂታል ግላዊ መረጃ አጠባበቅ ዙሪያ ያላትን ክፍተት ለመሙላት ከዓለም አቀፍ የግለሰብ መረጃ ስምምነቶች፣ ከህግ ማዕቀፎችና ፖሊሲዎች ጋር የተጣጣመ የአሰራር ስርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፤

4. በማንነት ላይ ያተኮረ በዲጂታል የሚፈፀሙ የሃይማኖትና የብሔር ማጥላላት፣ማንቋሸሽ፣ ፅንፈኝነት እና የመሳሰሉትን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር ማዕቀፎች መዘርጋት፤

   **ስልት አንድ፡** የዲጂታል የጥላቻ ንግግር፣ ፅሁፍ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የሚከለክል፣ አግባብነት ያለው የሳይበር አጠቃቀም የሚያበረታታ ደንቦችና አሰራር ስርዓት ይተገበራል፤

5. በሳይበር ምህዳር የታዳጊዎች ደህንነት ለመጠበቅ እና ለመከላከል የሚያስችሉ ህጋዊ ማዕቀፎች ይዘጋጃሉ፤ የአሰራር ስርዓቶችን ይዘረጋሉ፤ የአለምአቀፍ ትብብሮች ማሳደግና የአቅም ግንባታ ስራዎች መስራት፤

   **ስልት አንድ፡** የታዳጊዎች የዲጂታል መብት ጥሰት መከላከል የሚያስችል የክትትል አቅም እንዲኖር ይሰራል፣

   **ስልት ሁለት፡** ተቋማት በአወቃቀራቸው የታዳጊዎች ዲጂታል መብት እውቅና የሰጠ አወቃቀር እንዲኖራቸው ይሰራል፣

6. የሴቶችና ታዳጊዎች ሰብዓዊ ማንነት የሚመለከታቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በዲጂታል ማንነት ማኔጅመንት ዙሪያ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ፣ የህግ ማዕቀፎች ቀርፀው እንዲንቀሳቀሱ ድጋፍ ማድረግ፤

ስልት አንድ፡ በታዳጊዎችና ሴቶች የዲጂታል ማንነትና ግላዊ መረጃ ጥበቃ ለማጠናከር ማህበረሰቡን ያሳተፈ ህዝባዊ ንቅናቄዎች በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን፣ መድረኮች፣ ኮንፍረንሶች እና ወርክሾፖች ይዘጋጃሉ፤ የሳይበር ግላዊነት ደህንነት አስፈላጊነት ላይ እውቅና የሚሰጡ ሰፋፊ የምክክር መድረኮች ይመቻቻሉ፡

## 2.7. ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶች ጥበቃ

### 2.7.1. የፖሊሲ መግለጫ

በአሁኑ ዘመን በሃገራችን ኢንፎርሜሽን ውድ ሃብት እየሆነ በመምጣቱ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶችን እና ተቋማትን ከሳይበር ጥቃቶች መከላከል፤ የሳይበር ስጋቶችንና ተጋላጭነቶችን መቀነስ፤ የሳይበር ጉዳት ሲደርስ በፍጥነት መልሶ ማቋቋም አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ስለሆነም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በአግባቡ ለመምራትና ለመተግበር፣ ከውድመት ለመከላከል፤ እንዲሁም የሳይበር ምህዳሩን ደህንነት ለማረጋገጥ እና ተዓማኒነቱን ለማሳደግ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶች ጥበቃ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ መንግስት ለዘርፉ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በተጨማሪ በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ የሳይበር ክስተቶችንና ጥቃቶችን ለመከላከል መንግስት ከግሉ ዘርፍ ጋር በአጋርነት የደህንነት ቁጥጥሮችን በመጠቀም በቁልፍ መሰረተ-ልማቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ የሳይበር ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶችና አደጋዎችን ለመቋቋም የሚከተሉትን ግቦች እና ስትራቴጂዎች በመንደፍ ይሰራል።

### 2.7.2. ግቦች

ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ጥበቃ የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

1. ቁልፍ መሰረተ-ልማቶች እና ተቋማት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶች፣ ጥቃቶችና ውድመቶችን የመለየት፣ የመከላከል እና ምላሽ የመስጠት አቅም ማጎልበት፤

2. ከውጭ የሚገቡ እና በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማት ምርቶችና አገልግሎቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፤
3. ለቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶች ልዩ ጥበቃ ለማድረግ የመንግስት እና የግል ዘርፍ ትብብር እና ቅንጅት መፍጠር፤

### 2.7.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. ቁልፍ መሰረተ-ልማቶች እና ተቋማት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶች፣ ጥቃቶችና ውድመቶችን መለየት፤ መከላከል እና ምላሽ መስጠት የሚያስችሉ ተቋማዊ አቅሞችና መዋቅሮች መገንባትና የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤

    **ስልት አንድ፡** ቁልፍ የመንግስትና የግል ተቋማትን ሳይበር ደህንነት ሊያስጠብቅ የሚችል የተቀናጀ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ።

    **ስልት ሁለት፡** ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችንና ሊደርሱባቸው የሚችሉትን ጥቃቶችን የሚለይና አፋጣኝ መልስ የሚሰጥ አካል ይቋቋማል፤ ተቋሙን የሚያጠናክሩ የአሰራር ስርዓቶች እና አቅጣጫዎች ይዘረጋሉ፤

    **ስልት ሶስት፡** ብሔራዊ የቁልፍ መሰረተ-ልማቶች ደህንነት አመራር ስርዓት ይዘጋጃል፤ ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ በቀጣይነት ይሻሻላል፤

2. በቁልፍ መሰረተ-ልማቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመከላከል የሚረዱ ደረጃቸውን የጠበቁ የሳይበር ደህንነት ሕግጋትንና ስታንዳርዶቹን ለማልማት የሚያስችል አቅም መገንባት፤

    **ስልት አንድ፡** ቁልፍ መሰረተ-ልማቶችን ለመጠበቅ የመንግስት እና የግል ተቋማት ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁና ሀገራዊ አውድ ያገናዘቡ የሳይበር ደህንነት ሕግጋት፣ ፖሊሲዎች፣ ስታንዳርዶችና፣ ማእቀፎች ስራ ላይ ይውላሉ፤

**ስልት ሁለት፡** ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማት ተቋማት ዓለም-አቀፍ ይዘት ካላቸው የኢንፎርሜሽን ደህንነት ስታንዳርዶችና የአሰራር ሥርዓቶች ጋር የተጣጣመ መርሃ-ግብሮች እንዲቀርፁና የስራ ሂደቶቻቸው አካል እንዲያደርጉ ይደረጋል፤

**ስልት ሶስት፡** ለሚመለከታቸው አካላት በቁልፍ መሰረተ-ልማቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶች፣ ጥቃቶችና ውድመቶችን ለመለየት፣ ለመቀነስ፣ ለመከላከል እና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ወቅታዊነታቸውን የጠበቁ ትምህርቶች፣ ስልጠናዎች፣ የምክክር መድረኮች እና የመሳሰሉት ይዘጋጃል፤ ይሰጣል፤

**ስልት አራት፡** ለቁልፍ መሰረተ-ልማቶች የሚውሉ ሀገር በቀል የኢኮቴ ምርቶችን የማምረት አቅም ይገነባል፤

3. ደህንነታቸው የተረጋገጡ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማት ምርቶች፣ አገልግሎቶች፣ ፕሮቶኮሎችና የመገናኛ ዘዴዎች፣ አስተማማኝ አውታረ-መረቦችና ዲጂታል የቁጥጥር ሥርዓቶች ማልማት፤

**ስልት አንድ፡** ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማቶች፣ የኢኮቴ ምርቶች እና አገልግሎቶች ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ደህንነት ቴክኒካዊ ስታንዳርዶች ስራ ላይ ይውላል፤

**ስልት ሁለት፡** በማንኛውም ጊዜ የተጋላጭነት ፍተሻና የኢንፎርሜሽንና የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማት የደህንነት ኦዲት እንዲካሄድና ፈጣን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ይደረጋል፤

4. ለቁልፍ መሰረተ ልማቶች ልዩ ጥበቃ ለማድረግ የመንግስት፣ የግል ተቋማት እና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ሚናና ድርሻ ማሳደግ፤

**ስልት አንድ፡** ለቁልፍ መሰረተ ልማቶችና ስርዓቶች 24/7 አካላዊና ምናባዊ ጥበቃ ይደረጋል፤

**ስልት ሁለት፡-** ለቁልፍ መሰረተ-ልማቶች ልዩ ጥበቃ ለማድረግ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተግባራትና ኃላፊነቶች በመለየት ይሰጣል፤

## 2.8. ሃገራዊ እና ዓለም አቀፍ ትብብር

### 2.8.1. ሃገራዊ ቅንጅት እና አጋርነት

#### 2.8.1.1. የፖሊሲ መግለጫ

የሳይበር ደህንነት ጥቃት እጅግ ውስብስብ፣ ኢ-ተገማች፣ ተለዋዋጭና ድንበር የለሽ ከመሆኑ የተነሳ በመንግስትና በተወሰኑ ተቋማት ብቻ መፍትሄ የሚያገኝ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ ሃገራዊ ቅንጅት እና አጋርነት መመስረት፤ እንዲሁም በሳይበር ደህንነት ላይ የተጋረጡ ስጋቶችን መከላከል የሁሉም የባለድርሻ አካላት የጋራ ኃላፊነት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በተለይም የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎት ልማት በወሳኝነት የግሉን ዘርፍ የነቃ ተሳትፎ ይፈልጋል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የግሉ ዘርፍ በሀገሪቱ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ ልማት እንቅስቃሴ ዕድገት በማሳየት ላይ ቢሆንም የሳይበር ደህንነት ኢንዱስትሪውን ከማሳደግ አንጻር ያሉ ለውጦች ውስን በመሆናቸው የግሉ ዘርፍ ሀገሪቱ በሳይበር ደህንነት የምታደርገውን ጥረት በማፋጠን ረገድ ቁልፍ ሚና መጫወት እንደሚገባው መንግስት ይገነዘባል። ስለሆነም በሃገር ደረጃ የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ ሃገራዊ አቅሞችን አስተባብሮ ለመጠቀም የሚያስችል ቅንጅት እና አጋርነትን በማጠናከር እንዲሁም የግሉን ዘርፍ አስተዋጽኦ በማሳደግ ረገድ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የሚከተሉትን ግቦችና ስትራቴጂዎች በማስቀመጥ ይሰራል፡፡

#### 2.8.1.2. ግቦች

ሃገራዊ ቅንጅት እና አጋርነት የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፤

1. ሀገራዊ ሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ በመንግስት፣ በግሉ ዘርፍ እና በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅትና አጋርነት መመስረትና ማጠናከር፤
2. የሳይበር ደህንነት ምርት በማምረትና አገልግሎት በማቅረብ ላይ የተሰማሩ ሀገር በቀል የግል ተቋማት እንዲጨምሩና እንዲጠናከሩ በማድረግ የሀገሪቱን

የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎት ፍላጎት ከማርካት አልፈው በዓለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል፤

#### 2.8.1.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. በሀገራዊ ሳይበር ደህንነት ቁልፍ ሚና ያላቸው ሁሉም የመንግስት እና የግል ዘርፍ አካላት ተለይተው የሳይበር ደህንነት ቅንጅትና ትብብር ሥርዓት መዘርጋት፤

   **ስልት አንድ፡** የሳይበር ደህንነት ቅንጅትና እና አጋርነት የሚመራ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ይደረጋል፤

   **ስልት ሁለት፡** ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ፎረም ይቋቋማል፤

   **ስልት ሶስት፡** በሀገር ደረጃ የሳይበር ደህንነት ኮንፈረንሶች፣ ሴሚናሮችና መሰል ቅንጅትን የሚያጠናክሩ መርሃ ግብሮች በየጊዜው ይዘጋጃሉ።

2. ዜጎች፣ የግሉ ዘርፍ፣ የሲቪክ ማህበራትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሳይበር ደህንነት ጥቃትን ለመከላከል የሚጠበቅባቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማስቻል፤

   **ስልት አንድ፡** በባለድርሻ አካላት ዘንድ የድርሻና ኃላፊነት ግልጽነት ይፈጠራል፤

   **ስልት ሁለት፡** የሳይበር ደህንነት ባለድርሻ አካላት መካከል የልምድ ልውውጥና የዕውቀት ሽግግር ስርዓት ይዘረጋል፤

3. የድንገተኛ ኮምፒውተር አደጋዎች መከላከል ቡድን/ክፍል በሁሉም የመንግስት እና የግል ተቋማት መካከል የኢንፎርሜሽን ደህንነት አገናኝ ድልድይ ሆኖ እንዲያገለግል ይደረጋል፤

   **ስልት አንድ፡** የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት ድንገተኛ የኮምፒውተር አደጋዎች መከላከል ክፍል እንዲኖራቸውና በክስተቶች ዙሪያ የልምድ ልውውጥ እንዲኖር ይደረጋል፤

   **ስልት ሁለት፡** የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት ድንገተኛ የኮምፒውተር አደጋዎች መከታተያ ሥርዓታቸው ከብሄራዊ የኮምፒውተር አደጋዎች መከታተያ ሥርዓት ጋር የተቀናጀ እና የሚመጋገብ ይደረጋል።

4. ሀገር በቀል የሳይበር ደህንነት የግል ተቋማት እንዲጨምሩና እንዲጠናከሩ ማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፤

**ስልት አንድ፡** አዳዲስ ተቋማት እንዲፈጠሩና ያሉት ተቋማት እንዲጠናከሩ የሚያግዝ መርሃ ግብሮች ይቀረጻሉ፤ ተግባራዊ ይደረጋሉ፤

**ስልት ሁለት፡** ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚውሉ የሳይበር ደህንነት ውጤቶችን ለሚያመርቱ ተቋማት ድጋፍ ይደረጋል፤

**ስልት ሶስት፡** ደረጃቸውን የጠበቁ የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎቶች በሀገሪቱ ገበያ ቅድሚያ ማግኘት የሚችሉበት ድጋፍ ይመቻቻል፤

**ስልት አራት፡** በዓለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያግዝ ድጋፍ ይደረጋል፤

## 2.8.2. ዓለም አቀፍ ትብብር

### 2.8.2.1. የፖሊሲ መግለጫ

የሳይበር ደህንነት ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው በመሆኑ፤ ከምህዳሩ ተለዋዋጭነትና ድንበር የለሽነት ባህሪ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ስጋቶች፣ ተጋላጭነቶችና ጥቃቶች ለመከላከል ዓለም አቀፍ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስታንደርዶች፣ ልምዶች እና አመለካከቶች የተለያዩ በመሆናቸው የሳይበር ደህንነትን ከማረጋገጥ አንጻር ከፍተኛ ተጽዕኖ እያደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህ የተነሳ የሳይበር ስጋት፣ ተጋላጭነት እና ጥቃት ለመከላከል፤ የደህንነት ሁኔታን ለማጎልበት እና ደህንነቱ የተጠበቀ የሳይበር ምህዳር ለመፍጠር ዓለም አቀፍ ትብብር ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ስለሆነም የሃገራችን መንግስት ይህንን እውነታ በመገንዘብ የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ለማስቻል እና የተደራጀ የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ ስለላ፣ ጦርነትና የመሳሰሉ ብሄራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ ይዘት ያላቸው የሳይበር ወንጀሎችን ለመከላከል ይረዳ ዘንድ የዓለም አቀፋዊ ትብብር የፖሊሲ ትኩረት አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

#### 2.8.2.2. ግቦች

የዓለም አቀፍ ትብብር ማጠናከር የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

1. የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ ስለላ እና መሰል ዓለም-አቀፍ ይዘት ያላቸው የሳይበር ደህንነት ስጋቶች ለመከላከል ትብብር መፍጠር፤
2. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የሚደረግ ዓለም አቀፍ ትብብር የሃገሪቱ የውጪ ጉዳይ ዲፕሎማሲ አካል እንዲሆን ማድረግ፤
3. ሁለትዮሽና ከዚያ በላይ የሆኑ የሳይበር ደህንነት ስምምነቶችን ማበረታት እና ማጎልበት፤

#### 2.8.2.3. ስትራቴጂዎች እና ስልቶች

1. የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ ስለላ እና መሰል ዓለም-አቀፍ ይዘት ያላቸውን የሳይበር ደህንነት ስጋቶች በመከላከል ዙሪያ የሚፈጠሩ የሕግ ጥያቄዎችን ለመፍታት የሚያስችል የህግ ስርዓት ይዘረጋል፤

   **ስልት አንድ፡-** በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የሚኖሩ ዓለም-አቀፋዊ የትብብርና የአጋርነት ስምምነቶች እንደ አስፈላጊነታቸው ይፈረማል፤
2. ድንበር ተሻጋሪ የሳይበር ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ ስለላ እና የመሳሰሉትን ለመከላከል የሚያስችል በቴክኒካል እና በሕግ ማዕቀፎች የተቃኘ ዓለም አቀፍ ትብብሮች መመስረት፤

   **ስልት አንድ፡-** የሳይበር ጥቃቶችን ለመመከት ከተለያዩ ሀገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረግባቸው መንገዶች ይመቻቻል፤

   **ስልት ሁለት፡-** ድንበር ተሻጋሪ የሳይበር ወንጀሎች፣ ሽብርተኝነቶች፣ ስለላና መሰል ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ በሃገራት መካከል የመረጃ ልውውጥ እና የቴክኒካል ድጋፎች ይደረጋሉ፤

   **ስልት ሶስት፡-** የሳይበር ደህንነትን የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ አካል ሆኖ እንዲሰራበት ይደረጋል፤

3. ዓለም-አቀፍ የልምድ ልውውጥና የእውቀት ሽግግርን የሚያፋጥን የአቅም ግንባታ ሥርዓት መዘርጋት፤

**ስልት አንድ፡-** በሳይበር ደህንነት ጉዳዮች ላይ ብቃት ያላቸውን የሰው ኃይል ለመፍጠር ዓለም አቀፍ ስልጠናዎች ይመቻቻል፤

**ስልት ሁለት፡-** የግልና የመንግስት ተቋማት ከሌሎች ሀገራት መንግስታትና የግል ተቋማት ጋር ያላቸውን የሳይበር ደህንነት ቁርኝት ተገቢ በሆነ መልኩ እንዲያጠናክሩ ሁኔታዎች ይመቻቻል፤

**ስልት ሶስት፡-** የሳይበር ደህንነት ትብብር ለመፍጠር የሚያስችል ሃገራዊ አቅም ይገነባል፤

4. በሀገሪቱ ውስጥ የሚቀረጹ የሳይበር ደህንነት ሕጎችና ፖሊሲዎች ከዓለም-አቀፍ ይዘት ካላቸው የህግ ማዕቀፎችና ስታንዳርዶች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ማድረግ፤

**ስልት አንድ፡-** ዓለም-አቀፍ በሆኑ የሳይበር ደህንነት ትብብር መድረኮች ላይ ንቁ ተሳትፎ ይደረጋል፤

# ክፍል ሦስት

## የፖሊሲና ስትራቴጂ የአፈፃፀም ማዕቀፍ

### 3.1. አጠቃላይ ምልከታ

ይህንን ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ለማስፈፀም የተቋማት ድርሻና ሃላፊነት መለየት፣ አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ አወቃቀሮችን መዘርጋት፣ የክትትልና ግምገማ አሰራር መዘርጋት እንዲሁም የወደፊት አቅጣጫ ማመላከት አስፈላጊ ነው። ሳይበር ደህንነት በባህርዩ ውስብስብና እጅግ ተለዋዋጭ በመሆኑ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት በትብብርና በአጋርነት መስራት ያስፈልጋል። ስለሆነም የሳይበር ደህንነት ፖሊሲው ውጤታማ እንዲሆን የመንግስት፣ የግሉ ዘርፍ፣ የትምህርትና የምርምር ተቋማት፣ ማህበረሰባዊ ድርጅቶች (የሲቪክ ማኅበራት)፣ ሌሎች ሀገራዊ ባለድርሻ አካላትና እና የዓለም አቀፍ አካላት ተሳትፎን ይጠይቃል። ከዚህ አንፃር ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት ስትራቴጅካዊ አመራር ይሰጣል።

### 3.2. ተቋማዊ መዋቅር

በሃገራችን የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ ጠንካራ አቋም ያላቸው ተቋማት መፍጠርና ያሉትንም ማጠናከር ያስፈልጋል። መንግስት ይህንን በመገንዘብ ኢመደኤን ያቋቋመ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንግስት በሀገር ደረጃ እና በቁልፍ ተቋማት የሚከሰቱ የሳይበር ደህንነት ጥቃቶችን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚያገለግል ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ጥቃት መከላከል ግብረ ሃይል (ኢትዮ ሰርት) በማቋቋም የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ እየሰራ ይገኛል። ኢመደኤ ከተለያዩ ሀገራዊ ተቋማት ጋር በትብብርና በአጋርነት ሀገራዊ የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ በመስራት ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህንን ትብብርና አጋርነት ውጤታማ እና የተቀናጀ ለማድረግ ተቋማዊ መልክ ማስያዝ አስፈላጊ በመሆኑ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ያካተተ ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ምክር ቤት ይቋቋማል። የምክር ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም አባላት በህግ የሚወሰን ይሆናል። በተጨማሪም መንግስት ለፖሊሲው አፈፃፀም በሚያመች ሁኔታ በሀገር ደረጃና በዘርፍ (ሴክተር)

ደረጃ አዳዲስ ተቋማትን እና ግብረ ኃይሎችን ሊያቋቁም ወይም ባሉት ተቋማት ላይ ኃላፊነት ሊጨምር ይችላል።

### 3.3. የባለድርሻ አካላት ኃላፊነትና ሚና

ሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ያላቸው የግል ተቋማት ይህንን ፖሊሲና ስትራቴጂ የመተግበርና ተልዕኳቸውን መሰረት ያደረጉ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን ግዴታ አለባቸው። በተጨማሪ ከዚህ ፖሊሲና ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶች ጋር የሚጣጣም የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች የመንደፍና የመተግበር ኃላፊነት አለባቸው።

### 3.4. የፖሊሲና ስትራቴጂ ክትትል እና ግምገማ

የፖሊሲና ስትራቴጂውን ውጤታማነት በሁሉም ደረጃ ለመለካት እንዲቻል፤ እንዲሁም የፖሊሲውን አፈፃፀም ሂደት ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን ዓበይት ጉዳዮች ያካተተ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

1. የፖሊሲውና ስትራቴጂው ማስፈጸሚያ የድርጊት መርሃ ግብር በኢመደኤ ይዘጋጃል፤ ለአፈጻጸሙም የሳይበር ደህንነት ምክር ቤት የሚጠበቅበትን ሚና ይጫወታል፣
2. የመንግስትና የግል ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚመለከታቸውን በፖሊሲና ስትራቴጂው የተጠቀሱ ተግባራት እንዲሁም ፖሊሲና ስትራቴጂውን ለመተግበር በሚዘጋጁ ሌሎች ማዕቀፎች የሚካተቱ ተግባራት ማከናወናቸውን፣ አስፈላጊውን ተቋማዊ መዋቅር መዘርጋታቸውን እና ተፈላጊውን በጀትና ግብአት መመደባቸውን የሚያረጋግጥ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
3. በኢመደኤ አስተባባሪነት የፖሊሲና ስትራቴጂ አፈጻጸም ዙሪያ ኢንፎርሜሽን የማሰባሰብ፣ የማደራጀትና የመተንተን፤ እንዲሁም የሪፖርት ሥርዓት ይዘረጋል፤
4. የፖሊሲውንና ስትራቴጂውን አፈጻጸም ለመገምገም የሚረዳ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ አመታዊ ጉባዔ በኢመደኤ ይዘጋጃል፤

5. በሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራተጂ ክትትልና ግምገማ ውጤት መሰረት ሌሎች አስፈላጊ ማዕቀፎች የሚዘጋጁበት እና እንደ አስፈላጊነቱ ፖሊሲና ስትራቴጂው የሚሻሻልበት አቅጣጫ ይቀመጣል፤

### 3.5. የፖሊሲና ስትራቴጂው ህጋዊ ጉዳዮች

1. ይህ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በተወካዮች ምክር ቤት ሲፀድቅ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. ፖሊሲና ስትራቴጂው በሁሉም በዚህ ሰነድ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተመላከቱ አካላት ላይ ህጋዊ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡

### 3.6. የፖሊሲና ስትራቴጂው የፋይናንስ ጉዳዮች

1. ፖሊሲና ስትራቴጂውን ተፈጻሚ ለማድረግ እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስፈልገው የፋይናንስ አቅም በዋነኝነት ከመንግስት በሚመደብ በጀት ይሸፈናል፡፡

2. ለፖሊሲና ስትራቴጂው ማስፈጸሚያ የሚውለው በጀት በፖሊሲ ሰነዱ በተቀመጠው የክትትልና ግምገማ ስርዓት መሰረት ይህንን ፖሊሲ በበላይነት እንዲከታተል በህግ ሃላፊነት የተሰጠው አካል ውሳኔ መሠረት የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡

3. የፖሊሲውን ግቦች፣ ስትራቴጂዎችና ስልቶች ለማስፈጸም የሚቀረጹ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች እንደአስፈላጊነታቸው በሚመለከታቸው አካላት ትብብር የሚከናወኑ ይሆናሉ፡፡

### 3.7. የፖሊሲና ስትራቴጂ ስኬት አመላካቾች

1. የሃገሪቱን የሳይበር ደህንነት ስጋት፣ ተጋላጭነትና ጥቃት መቀነስ፤
2. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የተገነቡ በሀገራዊ፣ ዘርፋዊ እና ተቋማዊ አቅሞችና ስርዓቶች ማደግ፤

3. በሀገራዊ አቅም የተዘጋጁ የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎቶች መጨመር፤
4. ሳይበርን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መጠቀም የሚችል የነቃ ማህበረሰብ መፈጠር እንዲሁም በሀገሪቱ የሳይበር ደህንነት ባህል መፈጠር፤
5. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ የግሉ ዘርፍ ሚናና ኃላፊነት መጨመርና የግሉ ዘርፍ የሳይበር ደህንነት ምርት በማልማትና አገልግሎቶችን በማቅረብ ረገድ ቁልፍ አስተዋጽኦ ማበርከት፤
6. የሳይበር ደህንነት ሀገራዊ፣ ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ አጋርነቶች እና ትብብሮች ማደግና ተጨባጭ ሀገራዊ ጥቅም ማስገኘት፤

## 3.8. የፖሊሲና ስትራቴጂ ክለሳ

በሀገሪቱ ከሳይበር ደህንነት ጋር ተያይዞ በሚመጡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ቴክኖሎጂያዊ ተጽዕኖ ለውጦች፤ በዘርፉ የመንግስትና የግል ተቋማት ድርሻና ኃላፊነት እድገት ተከትሎ በሚፈጠሩ አዳዲስ ፍላጎቶች፤ እንዲሁም በፖሊሲው የክትትልና ግምገማ ውጤት መሰረት በሚሰጠው አቅጣጫ ይህ ፖሊሲና ስትራቴጂው ሊሻሻል ይችላል። በእነዚህ እይታዎች መነሻ የብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ጸድቆ ተግባራዊ ከሚሆንበት ጊዜ ጀምሮ ከሶስት እስከ አምስት ዓመታት ባሉት ጊዜያት ውስጥ ፖሊሲው ይከለሳል። የሳይበር ደህንነት ምክር ቤት የፖሊሲውን ክትትልና ግምገማ ውጤት መነሻ በማድረግ በሚያስቀምጠው አቅጣጫ መሰረት ኢመደኤ የፖሊሲና ስትራቴጂውን ክለሳ ሂደት የመምራትና የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት።